*ሚያዝያ 18 1998*

# ዴር ሱልጣንን በተመለከተ የአቋም መግለጫ

ኢትዮጵያውያን ለዘመናት በቆየው ታሪካዊ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ትስስር ምክንያት ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌምን ሁለተኛ ትውልድ ሀገራቸው አድርገው ይቆጥሯታል፡፡ ለዚህም ዛሬ በእስራኤል የሚገኙት ቅዱሳት መካናትና ጥንታዊ ቋሚ ይዞታዎች ህያው ምስክሮች ናቸው፡፡

እነዚህ ኢትዮጵያውያን በየጊዜው ሰላማቸውን የሚነሳው እና የእግር እሳት ሆኖ የሚያንገበግባቸው ጉዳይ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን እና በግብፅ ኮፕት ቤተክርስትያን መካከል ያለው የዴር ሱልጣን ገዳም የይገባኛል ጥያቄ ፍትሓዊ መፍትሄ ከማግኘቱ ይልቅ በስታትስኮ ምክንያት ለዘመናት መንተቱ ነው፡፡

ይህ የስታትስኮ ሕግ የባለቤትነት መብታችንን እንዳናገኝ ከማድረጉም በላይ በገዳሙ ውስጥ የሚኖሩትን አባቶቻችንና እናቶቻችንን ኑሮ አደጋ ላይ ጥሎታል፡፡ በተጨማሪም እንደ ቅዱስ ሚካኤል ያሉት ቤተመቅደሶቻችንና የመነኮሳቱ መኖሪያ ቤቶች በመፈራረስ ላይ ናቸው፡፡ ከሁሉም በላይ በዚህ ወቅት የግብፅ ኮፕቶች የጠብ አጫሪነት ሚና እየጨመረ እንዲመጣ ምክንያት ሆኖአል፡፡
በመሠረቱ የስታትስኮ ሕግ የሰብዐዊ መብቶችን አይነካም፡፡ ነገር ግን በመንፀባረቅ ላይ ያሉት ችግሮች የዚሁ አሉታዊ ሕግ ውጤት ናቸው፡፡

በአጠቃላይ በአሁኑ ጊዜ፡

1. **በገዳሙ ውስጥ የሚኖሩት አባቶቻችን እና እናቶቻችን ሰብዐዊ መብት ተገፏል**
2. **ቤተክርስትያናቱና በገዳሙ የሚገኙት መኖሪያ ቤቶች በመፈራረስ ላይ ናቸው**
3. **የግብፅ ኮፕቶች እንደከዚህ ቀደሙ ሁሉ በተደጋጋሚ ጠብ በመጫር እና አቅመ ደካማ መነኮሳት ላይ አደጋ ለማድረስ ይዝታሉ**

በዚህ መንፈስ አስቸኳይ ዓለምአቀፍ አስተባባሪ ኮሚቴ በማቋቋም ጠንካራ እርምጃ ለመውሰድ እንዲያመች የተለያዩ እንቅስቃሴዎች በአሜሪካ በአውሮፓና በእስራኤል ተጀመሯል፡፡ እናም ይህ አስተባባሪ ኮሚቴ በዴር ሱልጣንና በሌሎች ተመሳሳይ ጥያቄዎች ላይ በጋራ ለመስራት ተዘጋጅትዋል፡፡

እኛም በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም የምንገኝ ኢትዮጵያውያን እና የገዳሙ ወዳጆች በመተባበር የእስራኤል መንግሥት አስቸኳይ መፍትሄ እንዲሰጥ እና እርምጃ እንዲወስድ ለማሳሰብ ተገደናል፡፡

ስለዚህ እኛ በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም የምንገኝ ኢትዮጵያውያን እና የገዳሙ ወዳጆች **እሁድ ሚያዝያ 22 ቀን 1998 ዓ.ም ከጥዋቱ 3 ሰዓት** ወይንም እ.ኤ.አ **አፕሪል 30 ቀን 2006 ከጥዋቱ 9 ሰዓት** ጀምሮ በክቡር ጠቅላይ ሚንስትሩ ጽ/ቤት ፊት ለፊት ሰላማዊ ሰልፍ ይካሄዳል፡፡

በዚህ አጋጣሚ በመላው ዓለም የምትገኙ ኢትዮጵያውያንና የገዳሙ ወዳጆች ድጋፋችሁን እንድትሰጡ እና በአቅራቢያችሁ ለሚገኙ የእስራኤል ኤምባሲና ቆንስላዎች ከላይ የተገለፁትን ችግሮች በመጥቀስ የስልክ የፋክስ የኢሜል መልዕክቶች እንድታስተላልፉ በአክብሮት እንጠይቃለን፡፡

እኛም የዴር ሱልጣን አስተባባሪ ግብረ ኃይል አባላት በኢየሩሳሌም ከተማ የሚደረገውን የሰላማዊ ሰልፍ መደገፋችንን እናረጋግጣለን።

የዴር ሱልጣን አስተባባሪ ግብረ ኃይል አባላት፡

ዶ/ር መኮንን ባይሴ - አሜሪካ
አቶ ዳንኤል ዓለሙ - እስራኤል
አቶ ኪዳኔ ዓለማየሁ - አሜሪካ
አቶ ምስጢረ ኃይለ ሥላሴ - ስዊዘርላንድ
ዶ/ር ዮናስ ዘገየ - አሜሪካ
አቶ መክብብ ሰሎሞን - እስራኤል
አቶ ብርሃኑ ዓለማየሁ - አሜሪካ
ፕ/ር ማሞ ሙጪ - ዴንማርክ

ለተጨማሪ መረጃ በኢሜል አድራሻ፡ Dabresultan@yahoo.com